# በአገር ቤት በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ለመሰማራት ያሉ ምቹ ሁኔታዎች

1. መግቢያ

አገራችን የምትመራበት የኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂ የአገር ውስጥ ባለሀብት ዋነኛው የልማት ኃይል የሚሆንበትንና የውጭውን ባለሀብት ከአገር ውስጥ ባለሀብቱ ጋር በቅንጅት በኢኮኖሚው ውስጥ በማሳተፍ የኢንዱስትሪውን ልማት ማፋጠን የሚያስችል አቅጣጫ ተቀምጧል:: ይህንንም የተከተለ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች ተመቻችተዋል:: ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማት ለማምጣት ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ዕድገት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ወሳኝ መሆኑም ታምኗል:: አገራዊ ባለሀብቱ ለዚህ መሰረት ዋነኛ ተዋናይ ሊሆን እንደሚገባ በኢንዱስትሪ ልማት ስትራተጂው አቅጣጫ ተሰጥቶበታል::

## 2. የአገር ውስጥ ባለሃብት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ያለውን ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊነት

- የአገራዊ ባለሀብት ትራንስፎርሜሽን ዓላማ ባለሀብቱ በማኑፋክቸሪንግ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለው ተሳትፎ እመርታ እንዲያሳይና የአገር ዕድገት መሠረት በማድረግ፣
- የኢንዱስትሪው ዘርፍ በላቀ ደረጃ እንዲያድግና ከአገሪቷ አጠቃላይ ዓመታዊ ምርት (GDP) የሚኖረው ድርሻ ከፍ እንዲል ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ንቅናቄ በመፍጠር፣
- አገራችን በ2017 በቀላል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በአፍሪካ ቀዳሚ አገር እንድትሆን የተያዘውን አገራዊ ራዕይ ለማሳካት የሃገር ውስጥ ባለሃብቱ የማይተካ ሚና ስላለው በንቅናቄ ወደ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ እንዲገባ በማድረግ፣
- በአስመጪነት፣ ላኪነት እና በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለተሰማሩ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችንና ለዳያስፖራ ማህበረሰብ አባላት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ያለውን እድል በማስተዋወቅ በዘርፉ እንዲሰማሩ በማድረግ፣
- ሞዴል አርሶ አደሮች፣ በግብርና የተሰማሩ ማህበራት ከግብርና ዘርፎች ወደ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በብዛት እንዲሸጋገሩ ንቅናቄ በመፍጠር የኢንዱስትሪው ዘርፍ ደረጃ በደረጃ በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት የመሪነቱን ሥፍራ እንዲይዝ ማስቻልና ከዚህም ባለሃብቱ በየደረጃው በተሳትፎው ልክ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው::

## 3. በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለመሳተፍ የሚቻልባቸው የስራ መስኮች

- የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ፣
- የጫማ፣ ቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ፣
- አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ፣
- የኬሚካል እና ፋርማሲዩቲካልስ ኢንዱስትሪዎች፣

- የብረታ ብረት እና ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣
- የፓኬጂንግ ኢንዱስትሪ፣
- የኤሌክትሪካል እና ኤሌክትሮኒክስ ኢንዱስትሪዎች፣
- የባዮ- ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪ፣
- ፔትሮ ኬሚካል ኢንዱስትሪ፣

## 4. ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የተዘጋጁ የድጋፍ ፓኬጆች

### 4.1. የአዋጭነት ጥናቶች

#### ሀ) ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያስጠናቸው 10 ያዋጭነት ጥናቶች

- የተቀናጀ የቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የተቀናጀ የሰሊጥ ማቀናባበሪ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የተቀናጀ የበቆሎ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የተቀናጀ የጨርቃጨርቅ ምርቶች አከሰሰሪዎች ማምረቻ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የተቀናጀ የቆዳ ምርቶች አከሰሰሪዎች ማምረቻ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የሌብል ማምረቻ ፋብሪካ የአዋጭነት ጥናት፣
- የወረቀት ፓኬጅንግ ማምረቻ የአዋጭነት ጥናት፣
- የብረት ፓኬጂንግ ማምረቻ የአዋጭነት ጥናት፣
- የብርጭቆ ፓኬጂንግ ማምረቻ የአዋጭነት ጥናት፣
- የፕላስቲክ ፓኬጂንግ ማምረቻ የአዋጭነት ጥናት፣

### 4.2. መሬት፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች/ዞኖች እና ሌሎች መሰረተ ልማት አቅርቦት

#### ሀ) በክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የተዘጋጀ መሬት

በክልሎች እና በከተማ መስተዳድሮች 11,559.18 ሄክታር መሬት ለኢንዱስትሪ ዞን የሚውል መሬት ቢከለልም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ባደረገው የዳሰሳ ጥናት እስከ መጋቢት 2007 ዓ.ም. 4,863.62 ሄክታር መሬት ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ ቀሪው 7,300.94 ሄክታር መሬት (63.16 በመቶ) ባለሃብቶችን እየጠበቀ ይገኛል::

## ለኢንዱስትሪ ክለስተር ማዕከላት ግንባታ የመሬት ዝግጅት

እንደየከተሞቹ የዕድገት ደረጃና የአምራቾች ብዛት መሰረት ያደረገ ለኢንዱስትሪ ክለስተር ማዕከላት ለማምረቻ ህንጻዎች መገንቢያ የሚውል የመሬት ዝግጅት የማድረግ ተግባር በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች ይከናወናል፡፡

በዚሁ መሰረት በትልልቅ ከተሞች 250 ሄክታር፣ በመካከለኛ ዕድገት ደረጃ የሚገኙ ከተሞች 100 ሄክታር እንዲሁም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉት ደግሞ 50 ሄክታር መሬት የማዘጋጀት ተግባር በማከናወን ለእነዚህም የሚሆን ማስተር ፕላን በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህም በኢንዱስትሪ ፓርክና ክለስተር ልማት ኮርፖሬሽን እንዲተዳደሩ ይደረጋል፡፡

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለአራት የተቀናጁ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ፓይለት ፕሮጀክቶች በአራት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ ትግራይ) 1000 ሄክታር መሬት ተዘጋጅቷል፡፡

### ለ) ኢንዱስትሪ ፓርኮች

- በፌዴራል ደረጃ ለ11 ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚውል 7,687.7 ሄክታር መሬት ተከልሎ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
- ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን በተገኘው መረጃ ፓርኮቹ በዋናነት ኤክስፖርትን ታሳቢ አድርገው የሚለሙ ሲሆን፣ በዚህ መሰረት 20 በመቶ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች እና 80 በመቶ ለውጭ ባለሃብቶች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
- ፓርኮቹ በአሁኑ ወቅት በተለያየ የትግበራ ደረጃ ማለትም በመሬት ከለላ፣ በዲዛይንና ግንባታ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ግንባታቸው ተጠናቆ ስራ የጀመሩም ይገኙበታል፡፡

### ሐ) የሃይል አቅርቦት

- የሀይል አቅርቦትን በተመለከተ መንግስት በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ ዘመን ያጋጠሙ ጉድለቶችን መሰረት በማድረግ ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቅድሚያ ለመስጠት በተለይም የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና መንደሮችን በማማከል የከፍተኛ ሃይል አስተላላፊ መስመሮች እንዲያልፉ ተደርጎ እንደሚሰራ ታሳቢ የተደረገ ሲሆን፣ የግል ባለሃብቱ ኃይል አመንጭቶ እንዲሸጥም ተፈቅዷል፡፡ በዚህም፡-
- ኢንዱስትሪዎች የራሳቸውን ሰብስቴሽን በመገንባት ከብሄራዊ ግሪድ ሃይል እንዲወስዱ የማድረግ፣
- ኢንዱስትሪዎች ከ5 ሜጋ ዋት ጀምሮ በማመንጨት እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ ትርፉንም እንዲሸጡ የማድረግ፣
- ባለሃብቶች በሃይል ማመንጨት ኢንቨስትመንት እንዲገቡ የማበረታታት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡
- በዚህም መሰረት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን በተሻለ ሁኔታ ሃይል እንዲያገኙ ይሰራል፡፡

መ) ትራንስፖርት

- መንግስት በአለም አቀፍ ደረጃ በኤክስፖርት ተወዳዳሪ ለመሆን ተወደዳዳሪ የሆነ የትራንስፖርት ዋጋ እንሚያስፈለግ በማመኑ በመሰረታዊነት የባቡር ትራንስፖርት መሰረተ ልማት በተለያዩ የአገሪቱ ቀጠናዎች እየለማ ይገኛል።

- እየለሙ ካሉ የባቡር ኮሪደሮች መካከል የአዲስ አበባ ጅቡቲ ኮሪደር በ2009 በጀት አመት ስራ የሚጀምር በመሆኑ የትራንፖርት ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል።

- ከዚህ ጎን ለጎን በማኑፋከቸሪንግ ኢንዱስትሪ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን ለማበረታት ልዩ የየብስ ትራንስፖርት ታሪፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

- የኢትዮጵያ አየር መንገድ የካርጎ አገልግሎትም ኤክስፖርተሮችን ለማበረታታ ልዩ የካርጎ ታሪፍ በማውጣት ኤክስፖርትን እየደገፈ ይገኛል።

ሰ) የፋይናንስ አቅርቦት

- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ለመደገፍ መመሪያዎችን ያሻሻለ ሲሆን፣ በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የአሰራር ውስንነት የታየባቸውን መመሪያዎች በማሻሻል ከ2008 በጀት አመት ጀምሮ ተግባራዊ እያደረገ ነው።

- በዚህም የባንኩ የማበደር አቅም ጨምሯል። ተጨማሪ 175 ቅርንጫፎች ይከፈታሉ። የብድር ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች ተሻሽለዋል።

- ከላይ ከተጠቀሱት ማበረታቻዎች በተጨማሪ መንግስት ኤክስፖርተሮችን ለማበረታት ለሌተር ኦፍ ክሬዲት ሲከፈት ይከፈል የነበረውን የ3.5 በመቶ ክፍያ ወደ 0.5 በመቶ ዝቅ በማድረግ ድጋፍ አድርጓል።

4.3. የኢንቨስትመንት፣ የኤክስፖርት ማበረታቻ

- በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ለፕሮጀክቶቻቸው የሚያስፈልጉ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎችን (100 በመቶ) እና የካፒታል ዕቃ መለዋወጫዎችን (የካፒታል ዕቃውን ዋጋ 15 በመቶ) እንዲሁም ለሥራ የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ሌሎች ታክሶች በነጻ ከውጭ እንዲያስገቡ፣

- ፕሮጀክቶቻቸው ማምረት ሲጀምሩ እንደየፕሮጀክቶቻቸው ዓይነትና እንደሚቋቋሙበት ቦታ እየታየ ከ1 እስከ 9 ዓመት ድረስ ከገቢ ግብር ነጻ እንዲሆኑ፣ እንዲሁም

- ባለሀብቶቹ በተሰጣቸው የገቢ ግብር ነጻ ዘመን ውስጥ ኪሳራ ቢያጋጥማቸው የደረሰባቸውን ኪሳራ የገቢ ግብር ነጻ ዘመኑ ካበቃ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ወደፊት እንዲያስተላልፉ ይደረጋል።

- የነባር ኢንቨስትመንቶችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግና ማስፋፋቶችን ለማበረታታት ለአዳዲስ ኢንቨስትመንቶች የሚሰጡ ማበረታቻዎች በማሻሻያ አዋጁ ማስፋፊያዎችንም እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

- ከዚህም በተጨማሪም በኤክስፖርት ለተሰማሩ ድርጅቶ ግብዓት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ሌሎች ታክሶች ነጻ አድርገው እንዲያስገቡ የድጋፍ ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

## 4.4. የአቅም ግንባታና የሰው ኃይል አቅርቦት ድጋፎች

- የጨርቃ ጨርቅ እና አልበሳት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የምግብ፣ መጠጥ እና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የኬሚካል እና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- ብረታብረት እና ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣
- የአነስተኛ እና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ኤጀንሲ፣

## 4.5. የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅርቦት

- መንግስት የቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ እየተንቀሳቀሰባቸው ካለው ዘርፎች መካከል ለጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ፣ አግሮ-ፕሮሰሲንግ እና ለሌሎች የኢንዱስትሪዎች ግብዓቶች በስፋት የሚያቀርብና ኤክስፖርት የሚያደርግ የመንግስት ልማት ድርጅት እንደሚያስፈልግ በመገንዘቡ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅትን በማቋቋም ችግሮቹን ለመቅረፍ ሰፊ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡

- ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓትን በማልማትና የአቅርቦት ተግባራትን በማከናወን፣ የኢንዱስትሪ ግብዓት ምርትን በብዛትና በጥራት በማቅረብ ዘርፉን ተወዳዳሪና ውጤታማ በማድረግ እንዲሁም ተተኪ የኢንዱስትሪ ግብዓት ምርቶችን ለማምረቻ ተቋማት በማቅረብ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ወጪ ለማዳንም ሆነ ገቢ በማስገኘት ቀጣዩ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሳካ ለማገዝ ድርጅቱ ከሃገር ውስጥ ባለሃብቱ ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

## 4.6. የፕሮጀክቶች ድጋፍ

- በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚገኙ የኢ.ሲ.ፍ፣ ቲ.ቲ.ፍ.፣ ፒ.ሲ.ፒ. ፕሮጀክቶች ኤክስፖርትን ለመደገፍ ከአቅም ግንባታ ድጋፍ ጀምሮ፣ የውጭ ገበያ ፕሮሞሽን፣ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ፣ ዩ.ስ.ኤ.ድ እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለግል ሴክተሩ ድጋፍ ፓኬጆች አላቸው፡፡

- በቀጣይ እነዚህ ፕሮጀክቶች የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን በስፋት እንዲደግፉ በቅንጅት ይሰራል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ስለሆነም ቀጣይ የአገር ውስጥ ባለሃብቶች መፈልፈያና ምንጭ የሆኑ ብቃት ያላቸውን አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን ድግፎ በብዛትና በጥራት በመፍጠርና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በማስተሳሰር ገቢ ምርትን በሙተካትም ሆነ ለኤክስፖርት ከማምረት ረገድ በቂ ውጤት በሚያመጣ መልኩ በኢኮኖሚው ውስጥ በደረጃቸው ሊያበረከቱ የሚገባቸውን ድርሻ ማበርከት እንዲችሉ የተቀናጀና የተሟላ ድጋፍ ማመቻቸት የመንግስት የትኩረት ማዕከል እንዲሆን ተደርጎ እየተሰራበት ይገኛል።

ለበለጠ መረጃ የሚከተሉትን አድራሻዎች መጠቀም ይችላሉ። 1. www.moin.gov.et/home 2. https://www.facebook.com/Ethiopia.moi 3. http://www.ipdc.gov.et/index.php/en/

**ምንጭ፡-** በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ትራንስፎርሜሽን ዳይሪክቶሬት

## በዳያስፖራ አባላት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የጉምሩክ ስነ-ስርዓቶች

1. የካፒታል ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ስለማስገባት

- የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና የዚሁ አዋጅ ማስፈጸሚያ ደንብ ቁጥር 270/2005 የስነ ስርዓቱ ማስፈጸሚያ የህግ መሰረቶች ናቸው::
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከሰጣቸው የመንግስት መ/ቤት የቀረጥ ነጻ ፈቃድ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል::
- ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ ካፒታል እና የግንባታ ዕቃዎች ከነአከሰሰሪዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ናቸው::
- ዋጋቸው ከካፒታል ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ 15 በመቶ የማይበልጡ መለዋወጫዎችን ፕሮጀክቱ ማምረት ወይም አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይፈቀዳል::
- ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው የሚገቡ ተሽከርካሪዎች አይነትና ብዛት በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ዓይነትና ባህሪ መሰረት በመመሪያ ተወስኗል::
- የገቢ ግብር ወይም የግብር እፎይታ ማበረታቻ ጋር ተያይዞ በኢንቨስትመንት ዓይነት እና ቦታ መሰረት ከገቢ ግብር ነፃ የመሆን እንዲሁም ኪሳራን የማሸጋገር ጉዳዮች በደንብ ቁጥር 270/2005 እንዲስተናገዱ ይፈቀዳል::

2. ያለውጭ ምንዛሬ ዕቃዎችን ስለማስገባት

- የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 88/1995 እና የጉምሩክ መመሪያ ቁጥር 66/2004 የስነ-ስርዓቱ ማስፈጸሚያ የህግ መሰረቶች ናቸው::
- ዕቃዎች ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡበት አሰራር ፍራንኮ ቫሉታ የሚባል ሲሆን፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይተው ጠቅልለው ወደ አገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አንድ የግል አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ:: የዚህ መብት ተጠቃሚ ለመሆን ከነበሩበት ሀገር ያለው የኢትዮጵያ ሚሲዮን ጠቅልለው ለመግባታቸው የሚገልጽና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል::
- ለኢንቨስትመንት ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ባለሃብቶች አገር ውስጥ ከብር 5 ሚሊዮን ያላነሰ ኢንቨስት ማድረጋቸው እየተረጋገጠ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የሚያስፈልጓቸውንና ጠቅላላ ዋጋቸው ከ10000 የአሜሪካን ዶላር የማይበልጡ ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላሉ::

- በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ለመጀመሪያ ጊዜ የሚመጡ ግለሰቦች የሚያስገቧቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያዎች የንግድ መጠን የሌላቸው ዕቃዎች እስከ 5000 ከቀረጥ ነጻ ይገባል፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር የተሰጣቸው የመኖሪያ ፈቃድ እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም አግባብ ካለው መ/ቤት የተሰጠ ማረጋገጫ ያስፈልጋል፡፡

- ከውጭ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ምርት አምርተው ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶች ከውጭ የገቡ ጥሬ ዕቃዎች በአዋጅ ቁጥር 768/2004 መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ፡፡

- አምራች ድርጅቶች ከውጭ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ለሚያመርቱት ምርት በምርት ሂደት ወቅት በሀገር ውስጥ የታከለው ተጨማሪ እሴት መሰረት መመዘኛ መሰረት ካሟላ ለጥሬ ዕቃዎች የሁለተኛ መደብ ታሪፍ ቅናሽ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

- በፍራንኮ ቫሉታ እንዲያስገቡ የሚፈቀድላቸው አግባብ ባለው የመንግስት መ/ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያገኙ በውጭ አገር በዘላቂነት የሚኖሩ ኢትዮጵያያንና የውጭ ዜግነት ያላቸው የኢትዮጵያውያ ተወላጅ ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ስራቸው የሚሆን የካፒታል ዕቃ፣ ጥሬ ዕቃ እስከ ኮሚሽኒንግ ደረጃ የሚበቃ እና ለግል መገልገያ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች፣

- ለቤተሰብ፣ለዘመድና ለጓደኛ ከውጪ ሀገር በስጦታና በልገሳ ወደ አገር የሚገቡ የንግድ መጠን የሌላቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች፣

- በማንኛውም መስከ ላለ ተመራማሪ ከምርምር ስራው ጋር የተያያዘ በስጦታ ወይም በልገሳ የተገኙ ዕቃዎች፣

- የኃይማኖት፣ የትምህርት፣ የህክምና ወይም የሞያ ተቋማት/ድርጅቶች ለተቋሞቹ ወይም ድርጅቶቹ ተግባራት ብቻ የታቀዱ በስጦታ ወይም በእርዳታ ከውጪ አገር የሚያስገቧቸው ለንግድ የማይውሉ ዕቃዎች፣

- ለቤተሰብ፣ ለዘመድና ለጓደኛ ከውጪ ሀገር በስጦታና በልገሳ ወደ አገር የሚገቡ የንግድ መጠን የሌላቸው ተሽከርካሪን የማይጨምር የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች (FOB 1000 USD)፣ (ነገር ግን ያገለገሉ አልባሳትና ጫማዎችን ማስገባት አይፈቀድም፡፡ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስገባት አይፈቀድም፡፡) በልዩ ሁኔታ ፍራንኮ ቫሉታ እንዲገቡ ይፈቀዳል፡፡

3. በጉምሩክ በኩል ለዳያስፖራዎች ያሉ ምቹ ሁኔታዎች

❖ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/06 ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎች ተካተዋል፡፡ (Pre-arrival clearance, simplified procedure, electronic declaration, reduced document requirement)

❖ ለኢንቨስትመንትና ፕሮጀክት የሚገቡ ዕቃዎች ተለይተው አንድ መስኮት የተቋቋመላቸው ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ በአንጻራዊ የተሻለ የመፈፀም አቅም ያላቸው ባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡

❖ ለሚያስመጧቸው የካፒታል ዕቃዎች እና የምርት ግብዓቶች በፕሮጀክት ቦታው እንዲፈተሽላቸው ተፈቅዷል፡፡

- ኢንቨስተሮች ባላቸው የህግ ተገዥነት መነሻ ከሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በማጥናት ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት (ፈጣንና ወጪ ቆጣቢ) ይሰጣል፡፡
- ምርት አምርተው ለውጪ ገበያ ለሚልኩ ኤክስፖርተሮች አንድ መስኮት (የወጪ ንግድ ማበረታቻ ዩኒት) ተቋቁሟል፡፡ እንዲሁም ለወጪ ዕቃ ማምረቻ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይፈቀዳል፡፡
- በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆነው የምርት ሂደታቸውን አጠናቀው ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ ዕቃዎች ተመርተው ለሽያጭ እስከሚውሉ ድረስ ከውጪ በገቡ ጥሬ ዕቃዎች ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ ሳይከፈል ይቆያል፡፡
- በኢንዱስትሪ ፓርክ እና ዞን ሙሉ የጉምሩክ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

4. ሊማሉ የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
- ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የቀረጥ ነፃ ደብዳቤ፣
- ከዲክለራሲዮን ጋር አባሪ ሆነው የሚቀርቡ ሰነዶች፡- የዋጋ ሰነድ፣ የማጓጓዣ ሰነድ፣ የዕቃ ዝርዝር መግለጫ ሰነድ፣ የስሪት አገር የምስክር ወረቀት፣ የባንክ ፈቃድ፣
- ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች በማሟላት ዲክለራሲዮን እንዲሞላ ለጉምሩክ አስተላላፊ መስጠት፣

# የዳያስፖራ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር (TIN) ምዝገባ ስርዓቶች

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በውጪ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የግብር ከፋይነት ምዝገባ አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበትን በጣት አሻራ የተቀናጀ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ ስርአት (Offline Tin Registration) ዘርግቶ ኢ.ኤ.አ. ከ2010ዓ.ም. ጀምሮ በሰሜን አሜሪካ (ዋሽንግተን ዲሲ እና ሎስ አንጀለስ) እንዲሁም ካናዳ (ቶሮንቶ) በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች አማካይነት ለዳስፖራው አባላት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

- ይሁንና ይህ ስርዓት በተለያዩ ሀገራት ካለው የአገልግሎቱ ፈላጊ የዳያስፖራ አባላት ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ተደራሽነቱ እጅግ ውስን መሆኑ አጠያያቂ ባለመሆኑ ባለስልጣን መ/ቤቱ ይህንን ስርዓት የበለጠ በማጠናከርና ሌላ የተሻለ ተደራሽነት ያለው ተጨማሪ ስርዓት በመቅረጽ ኢ.ኤ.አ. ከ2014 ዓ.ም. ጀምሮ በሁለት መንገዶች የዳያስፖራ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል። እነርሱም ቀጥተኛ ያልሆነ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ ስርዓት (Offline Tin Registration) እና የርቀት የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ ስርዓት (Remote Tin Registration) ናቸው።

## 1. ቀጥተኛ ያልሆነ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ ስርአት(Offline Tin Registration)

የተቀናጀ የመንግስት ታክስ አስተዳደር (SIGTAS) ተደራሽነት እና የቴሌ ኔትወርክ ሽፋን በሌለበት አካባቢ በተንቀሳቃሽ የአሻራ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት ምዝገባ የሚካሄድበት ስርዓት ነው። ይህን አገልግሎት ለማግኘት

1. ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚገልፅ ፓስፖርት ኮፒ መያዝ፣
2. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ደግሞ የትውልደ ኢትዮጵያዊነት መለያ መታወቂያ ኮፒ በመያዝ የአሻራ መቀበያ ማሽኖች በተቀመጡባቸው የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ወይም ቆንጽላ ጽ/ቤቶች በመገኘት ለምዝገባ የተዘጋጀ ቅጽ መሙላትና አሻራ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።
3. በምዝገባ ወቅት የሚሰጣቸውን የአሻራ መለያ ቁጥር (Application No.) ኢትዮጵያ ለሚገኝ ህጋዊ ተወካይ መላክ፣
4. ተወካዩ የአሻራ መለያ ቁጥሩን፣ ህጋዊ የውክልና ማስረጃውንና ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ኮፒ ይዞ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በአካል በመቅረብ ወይም በዳይሬክቶሬቱ ፋክስ ቁጥር (00251-11 515 64 61) በመላክ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እንዲያገኝ ይደረጋል።

## ቀጥተኛ ያልሆነ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ምዝገባ ስርዓት (Offline Tin Registration) ጠቀሜታዎች

- ምዝገባው ተንቀሳቃሽ የጣት አሻራ ምዝገባ ማሽኖች ባሉባቸው ማዕከላት የሚከናን በመሆኑ ፈጣንና ጥራት ያለው ነው።

- የባለጉዳዩ የጣት አሻራ መረጃ በቀጥታ ካለበት ተወስዶ ወደ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የመረጃ ቋት በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲገባ ስለሚደረግ አገልግሎቱ ፈጣን ነው።

➢ ለግንዛቤ እስካሁን ድረስ የምዝገባው አገልግሎት እየተሰጠ ያለው በአሜሪካና ካናዳ በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ብቻ በመሆኑ ተደራሽነቱ ውስን ቢሆንም አገልግሎቱ ከተጀመረበት እ.ኤ.አ. ከ2010 ጀምሮ እስከ ሜይ 2016 ድረስ ለ19,601 የዳያስፖራ አባላት አገልግሎቱን መስጠት ተችሏል፡፡

2. የርቀት የጣት አሻራ ምዝገባ ስርአት (Remote TIN Registration System)

- ✓ በመላው አለም ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አባላት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ምዝገባ አገልግሎት የተዘጋጀ ስርዓት ሲሆን፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድረ-ገጽ (www.erca.gov.et) ላይ የተቀመጡ የግል መረጃ መሙያ እና አሻራ መስጫ ቅጾችን በማውረድና print በማድረግ በኤምባሲዎች (ቆንስላ ጽ/ቤቶች) እና ወንጀል ምርመራ ፖሊስ ጣቢያዎች አሻራ የሚሰጥበት፣ የሚመለከተው የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ቆንስላ ጽ/ቤት) ካረጋገጠው በኋላም ወደ ባለስልጣኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት ተልኮ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር የሚያገኙበት አሰራር ነው፡፡ ይህንን አገልግሎት ለማግኘት፡-
- ✓ ወደ ባለስልጣ መ/ቤቱ ድረ-ገጽ (www.erca.gov.et) በመግባት የጣት አሻራ እና የግል መረጃ መመዝገቢያ ቅጾችን በማውረድ በተለይም የጣት አሻራ መቀበያ ቅጹን በ(A4size) ማተም ያስፈልጋል፡፡
- ✓ ቅጾችን በመያዝ ወደ ኤምባሲዎች (ቆንስላ ጽ/ቤቶች) ወይም አቅራቢያው በሚገኝ የወንጀል ምርመራ ፖሊስ ጣቢያ በመገኘት አሻራ መስጠት ይጠበቃል፡፡
- ✓ የአመልካቹ የተሟላ ማስረጃ (ሀርድ ኮፒ) በሚመለከተው የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ቆንስላ ጽ/ቤት) ማረጋገጫ ከተሰጠበት በኋላ ኢትዮጵያ ለሚገኝ ህጋዊ ወኪል ወይም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይላካል፡፡
- ✓ የአመልካቹ ማስረጃ  በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ማረጋገጫ ተሰጥቶበ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ይላካል፡፡
- ✓ የመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬትም የመጣለትን ማስረጃ በባለጉዳዩ ህጋዊ ወኪል አረጋጋጭነት መረጃውን አጥርቶ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡
- ✓ የግብር ከይነት መለያ ቁጥሩ (ቲን) ወደሚፈለገው የግብር መከፈያ ማዕከል በሲስተም ይላካል፡፡
- ✓ ይህ የርቀት የግብር ከፋይ ምዝገባ አገልግሎት መሰጠት ከጀመረበት እ.ኤ.አ. ከ2014 ጀምሮ እስከ ሜይ 2016 ድረስ 130 ኢትዮጵያዊያን የዳያስፖራ አባላት የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

የርቀት የጣት አሻራ ምዝገባ ስርአት (Remote TIN Registration System) መሰረታዊ ጠቀሜታዎች

- ☞ የኢትዮጵያ ኤምባሲ (ቆንስላ ጽ/ቤት) ባሉባቸው ሀገራት ለሚገኙ ዜጎች ሁሉ ተደራሽ ነው፡፡
- ☞ ብዙ ወጪ ሳያስወጣ አገልግሎቱን ማዳረስ ያስችላል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥሮች 00251-115-51 58 08፣ 00251-115-52 90 87፣ 00251-115-51 53 17 መጠየቅ እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንን ድረ-ገጽ (www.erca.gov.et) መጎብኘት ይችላሉ፡፡

ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

# የመንግስት ቤቶች አስተዳደር የተሻሻለ መመሪያ

1. መግቢያ

- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይዞታ በኪራይ መልክ ለመኖሪያ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ የመንግስት ቤቶቹ ለረጅም ዓመታት ትኩረት ያልተሰጣቸው በመሆኑ መረጃቸው በአግባቡ ያልተደራጁ ከመሆናቸውም ባሻገር አገልግሎት እየሰጡና የፈረሱ መኖሪያና ንግድ ቤቶች ያሉበት ሁኔታ በአግባቡ ባለመለየቱ ምክንያት ለቁጥጥርና ክትትል አመቺ ባለመሆናቸው በስፋት ለህገ ወጥ ድርጊት የተጋለጡ ናቸው፡፡
- እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ በ1996 እና በ2004 ዓ.ም የከተማው አስተዳደር የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ደንብ ከማውጣቱ ባሻገር ቤቶችን በማዕከላዊነት የሚከታተልና የሚያስተዳድር ተቋም የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ቢቋቋምም ኤጀንሲው በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመንግስት ቤቶች አስተዳዳር መመሪያ በማዘጋጀት ቤቶችን አንድ ወጥ በሆነ አሰራር ለማስተዳደር የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም የተደራጀ መረጃ አለመኖርና የመኖሪያና ንግድ ቤቶች በአግባቡ አለማስተዳደር ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት መሙላት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ አበባ ከተማ የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀፅ 25 መሰረት የመንግስት ቤቶች አስተዳደር የተሻሻለ መመሪያ አውጥቷል፡፡
- የመመሪያው ፍሬ ሃሳቦች እንደሚከተለው አጠር ባለ መልኩ ቀርበዋል፡፡

**2. የቀበሌ ንግድ ቤት ለሶስተኛ ወገን ስለማስተላለፍ**

የቀበሌ ንግድ ቤትን በኪራይ የመጠቀም መብት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፡፡ ሆኖም ሊተላለፍ የሚችለው ከዚህ በታች በተቀመጠው አግባብ ብቻ ይሆናል፡-

ሀ. የንግድ ቤት ተከራይ በሞት ሲለይ ለህጋዊ ባል ወይም ሚስት፣

ለ. የንግድ ቤት ተከራይ እና የትዳር ጓደኛው በሞት ሲለዩ የሟች ህጋዊ ወራሽ ልጅ/ልጆች በንግድ ቤቱ የሚተዳደሩ መሆኑን እና ከዚህ ውጭ ሌላ መተዳደሪያ የሌላቸው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ. በፍርድ ቤት ወይም በመንግስት ወይም በከተማው አስተዳደር ውሳኔ ሲሰጥበት እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡ የስም ዝውውርን በተመለከተ አግባብ ባላቸው ሕጎች የሚመራ ይሆናል፡፡

መ. ለሶስተኛ ወገን የሚተላለፍለት አካል ምንም ዓይነት ሌላ/የንግድ ቤት፣ ቦታና መኖሪያ ቤት የሌለው ስለመሆኑ ፈርሞና ተጣርቶ ብቻ ይሆናል፡፡

**3. ከልከላና ተጠያቂነት**

**3.1. የቀበሌ መኖሪያ ወይም ንግድ ቤት ወይም የአስተዳደሩን ቤት ስለማስረከብ**

ሀ. ማንኛውም የቀበሌ መኖሪያ ወይም ንግድ ቤት ወይም የአስተዳደሩን ቤት ከአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ የተከራየ ሰው የራሱን ቤት ከገነባ ወይም የጋራ ህንፃ ቤት ከገዛ ወይም የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ቤት ካገኘ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት ቤቱን የለቀቀ ከሆነ ቤቱን ባለበት ሁኔታ ለኤጀንሲው ማስረከብ ይኖርበታል፡፡

ለ. ኤጀንሲው ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ቤቱን ከተረከበ ተከራይ መሸኛ ወይም ማስረጃ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ውዝፍ ዕዳ የሌለበት መሆን ተረጋግጦ መሸኛ እንዲሰጠው ይደረጋል::

## 3.2. የተከለከሉ ድርጊቶች /የተከራይ ግዴታዎች/

ማንኛውም ተከራይ ወይም ይህን መመሪያ የሚያስፈጽም አካል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች ማከናወን የተከለከለ ነው::

ሀ. ማንኛውም ሰው በህጋዊ መንገድ በተከራየው ቤት ውስጥ ባለ ክፍት ቦታም ሆነ በቤቱ አካል ላይ ካለ አስተዳደሩ ፈቃድ ግንባታ መገንባት ከልክል ነው::

ለ. ከኤጀንሲው ፈቃድ ወይም ከውሉ ውጭ የቤቱን አገልግሎት መለወጥ የተከለከለ ነው::

ሐ. ከኤጀንሲው የተከራየውን የመንግስት ቤት ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው::

መ. ከአስተዳሩ የተከራየውን ቤት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ማከራየት የተከለከለ ነው::

ሠ. ማንኛውም ተከራይ ከተሰጠው የእድሳት ወይም ጥገና ፈቃድ ውጭ የቤቱን ቅርጽ፣ እና ስፋት መቀየር አይችልም፣ በሕገወጥ መንገድ የተያዙ መኖሪያና ንግድ ቤቶች እርምጃ ተወስዶ ለሕጋዊ አካላት የማስረከብ ግዴታ አለባቸው::

ረ. የመንግስት ቤትን ከኤጀንሲው ፈቃድ ውጭ ያለውል መያዝ የተከለከለ ነው::

ሰ. በዚህ መመሪያ በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደው ውጭ የቀበሌ ወይም የመንግስት ንግድ ቤቶችን ካለጨረታ ማስተላለፍ ከልክል ነው::

ሸ. ከኤጀንሲው የተከራየውን የቀበሌ ወይም የመንግስት ቤት ወይም ህንፃ ዲዛይን መቀየር የተከለከለ ነው፣ የኤጀንሲው ሠራተኞች በማንኛውም ወቅት ስለቤቱ ቁጥጥርና መረጃ ለመጠየቅ ለስራ ጉዳይ ሲንቀሳቀሱ የመተባበርና ስለቤቱ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት::

ቀ. ከኤጀንሲው የተከራየውን ቤት ኪራይ ሳይከፍሉና ውል ሳያሳድሱ መገልገል የተከለከለ ነው::

በ. ለመንግስት ሹመኞች በኪራይ የተሰጡ/የተመደቡ ቤቶችን በግል ወይም በተጃሚ ስም ማዋዋል የተከለከለ ነው::

ተ. ኤጀንሲው የመንግስት ህንፃዎች ምዝገባ ለማካሄድ ለሚያደርገው ጥረት መረጃ አለመስጠት ወይም መደበቅ የተከለከለ ድርጊት ነው፣

ቸ. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ ከሚፈቀደው ውጭ የመንግስት ቤትን ማከራየት፣ መጠቀም፣ ማስተላለፍ፣ ኪራይ መሰብሰብ ከልክል ነው:: ከ2 ወር በላይ ዘግቶ ማስቀመጥ አይፈቀድም::

ነ. የመንግስት ቤት የሚከራየው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው እና ለተማው ነዋሪ ብቻ ነው::

ኘ. የውኃ፣ የመብራትና የስልክ የተጠቀሙበትን ለየተቋሙ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

## 3.3. በመኖሪያ ቤትም ሆነ በንግድ ቤቶች ውል ስለማቋረጥ

ሀ. ተከራይ ከውል ውጭ ቤቱን ሙሉ ለሙሉ ለሶስተኛ ወገን ያስተላለፈ እንደሆነ፣ ህገወጥ ግንባታ ከገነባ፣ ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የአገልግሎትና የዘርፍ ለውጥ ካደረገ እና በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው ውጪ የህብረተሰቡን ደህንነትና ጤንነት የሚጎዳ ተግባር ማከናወኑ ሲረጋገጥ ውሉ ሊቋረጥ ይችላል፡፡

ለ. ማንኛውም ተከራይ ለተከታታይ 6 ወራት የቤት ኪራዩን ባይከፍል ኤጀንሲው ውሉን ያቋርጣል፡፡ ሆኖም ውል ከመቋረጡ በፊት ለተከራይ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊደርሰው ይገባል፣ለ3ኛ ወገን ካስተላለፈ ፣ቤቱን አለአግባብ ከያዘ፣ ያለውል የኤጀንሲውን ቤት መያዝ፣ የውል ዕድሳት አለማድረግ፣ ሁለት የመንግስት ቤት መያዝ፣ የግል ቤት እያለው የመንግስት ቤት መያዝና በኤጀንሲው ቤት/ቦታ/ ካርታ ማውጣት፣ ቤቶቹን ያለአገልግሎት ዘግቶ ማስቀመጥ፣ ቤቱ ለመንግስት ሲፈለግ፣ የውል ዘመን ሲፈጸም፣ ቤቱ ሲፈርስ፣ ከሃገር ውጭ የወጣና እንደማይመጣ ሲረጋገጥና ሌሎች የውል ግዴታዎችን አለመወጣት ሲያጋጥም አከራይ የ30 ቀናት ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉ ይፈርሳል፣ ቤቱንም ይረከባል፡፡

ሐ. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ውል የተቋረጠበትን ተከራይ ውዝፍ የቤት ኪራይ ዕዳ እና ሌሎች ኤጀንሲው ያወጣቸውን ወጪዎች በሕግ ጠይቆ እንዲከፈለው ያደርጋል፡፡ ሆኖም ኤጀንሲው የውል ማቋረጥ ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ተከራይ ያለበትን መሰረታዊ ችግሮች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተከራይን ውል ማቋረጥ ከህብረተሰብ ሞራል ጋር ተቃራኒ ሆኖ ካገኘው እና ተከራይን ለከባድ ችግር የሚያጋልጥ ከሆነ ውዝፍ እዳውን በስድስት ወር በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 3.4. ተጠያቂነት

ሀ. ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ በወንጀልም ሆነ በፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

ለ. ከመንግስት ቤቶች አስተዳደርና ተያያዥ ስራዎችን የሚሰራ ማንኛውም አስፈፃሚና ፈፃሚ ሠራተኛ ወይም የስራ ኃላፊ በዚህ መመሪያ የተደነገጉ ግዴታዎችና ክልከላዎችን ተላልፎ ከተገኘ በወንጀልና በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ሠራተኞች አዋጅና በአቤቱታ ቅሬታ አፈታት ሥርዓትና ተጠያቂነት ደንብ ቁጥር 48/2004 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡